# የአማርኛ ትምህርት የፈተና መለማመጃ ጥያቄዎች

## ክፍል አንድ

1. ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ቃላት መካከል የተግብሮ ቃል የሆነው የቱ ነው?

   ሀ) ገዛ ለ) ተገዛ ሐ) ገዛች መ) ገዙ

2. ሁለት ዓ/ነገር መሆን የሚችሉ ቅንጅቶች በአያያዦች በአንድ ዓ/ነገር ተጠቃለው ሲቀርቡ ምን ዓይነት ዓ/ነገር ይባላል?

   ሀ) ነጠላ ዓ/ነገር ለ) ድብልቅ ዓ/ነገር

   ሐ) ድርብ ዐ/ነገር መ) ድርብ ድብልቅ

3. የአማርኛ ሰዋሰው ትምህርት በተለያዩ ደረጃ በትምህርት ቤት ሲሰጥ ቆይቷል፤................ ለትምህርት የሚረዱ አጋዥ የሰዋሰው መፅሃፍት በየደረጃው እየተዘጋጁ ሲቀርቡ ብዙ አይታይም። በቦታው ሊገባ የሚችለው አያያዥ የቱ ነው ?

   ሀ) ስለዚህ ለ) አለበለዚያ ሐ) ስለሆነም መ) ይሁን እንጂ

4. ከዚህ በኋላ ብቸኝነት ቀርቶብኝ **<u>ውሃ አጣጭ</u>** ልፈልግ። የተሰመረበት ቃል ዓውዳዊ ፍቺ፡

   ሀ) ሠራተኛ ለ) እህት ሐ) እናት መ) የትዳር አጋር

5. **<u>እህል ውሃ ቀመሰ</u>** የሚለውን አገላለጽ ከሚከተሉት አማራጮች ከየትኛው ጋር በትርጉም ሊስማማ ይችላል?

   ሀ) አፉን አሟሸ ለ) አፉን አበስ ሐ) አፉን ዘጋ መ) አፉን አጣፈጠ

LIVEWORKSHEETS

6. ከበደ የትምህርት ቤት **<u>ዝንባሌው</u>** ዝቅተኛ ነው ። ለተሰመረበት ቃል በፍቺ የሚስማማው:-

ሀ) ጭንቀቱ　ለ) ዕቅዱ　ሐ) ጥረቱ　መ) ፍላጎቱ

7. ፈዛዛ ብሎ ደማቅ ቢል አናት ብሎ ምን ይላል?

ሀ) መሃል　ለ) ጣሪያ

ሐ) ግርጌ　መ) ጎን

8. የቃላት ስውር ወይም ድብቅ ፍቺ ነው ።

ሀ) እማሬያዊ ፍቺ　ለ) ፍካሬያዊ ፍቺ

ሐ) ዐውዳዊ ፍቺ　መ ) ሁሉም

9. አንድ ሰው የሚፈጽመውን ድርጊት ወይም ተግባር የሚገልጹ ............ ይባላሉ

ሀ) ገቢር ግሶች　ለ) ተገብሮ ግሶች

ሐ) መስተፃምር　መ) ቅፅል

10. ከደብረሲና የመጣ **<u>የገብስ</u>** ቆሎ በላሁ ። የተሰመረበት ሐረግ ............ ነው ።

ሀ) ቅጽላዊ ሐረግ　ለ) ተውሳከ ግሳዊ ሐረግ

ሐ) ስማዊ ሐረግ　መ) መስተዋድዳዊ ሐረግ

11. ሰዎቹ ተሰብስበው **<u>በለሆሳስ</u>** ይነጋገራሉ ። ለተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ ፍቺ የሚሆነው ፡

ሀ) በችኮላ　ለ) በፍጥነት

ሐ) በሹክሹክታ　መ ) ሀ እና ለ

12. የአንድን ነገር ቀለም፣ እንቅስቃሴ፣ ድምጽ የሚገልጽልን የድርሰር ዓይነት፡

LIVEWORKSHEETS

ሀ) ተራኪ ለ) ገላጭ

ሐ) አመዛዛኝ መ ) ሰዕላዊ

13. የሀሳብ ቅደም ተከተልን በቅድሚያ ለመወሰን እና ለማቀናበር የሚረዳው የቱ ነው ፡፡

ሀ) አስተዋጸኦ ለ) ቢጋር

ሐ) ድርሰት መ) ሀ እና ለ

14. ብዙ ሰዎች በተለያየ ምክንያት ከኖሩበት ............... ሊሰደዱ ይችላሉ። ባዶ ቦታዉን ሊያሟላ

የሚችለው ቃል፡

ሀ) ጉፍታ ለ) ጥሩር ሐ) ቀዬ መ) ማር

15. ተማሪዎች የእግር ኳስ ጨዋታ እያካሄዱ ነው ፡፡ ይህ አረፍተ ነገር በየትኛው የጊዜ አይነት የተገለፀ ነው ?

ሀ) የትናንት ለ) የኃላፊ ሐ) የአሁን መ) የወደፊት

16. የንግግር ክሂል ለማዳበር ከሚረዱ ብልሃቶች መካከል ልዩ የሆነው፡

ሀ) ቃል መጠይቅ ለ) ጭውውት

ሐ) የቃል ሪፖርት መ) የፅሁፍ ሪፖርት

17. ከበሮ ይመታል ከተባለ ነጋሪት............ ይባላል፡፡

ሀ) ይደበደባል ለ) ይጨሃል

ሐ) ይጎሰማል መ) ይደለቃል

18. የሂሳብ ትምህርት እወዳለሁ............... ጥሩ ውጤት አላመጣሁም። ይህንን ዓረፍተ ነገር

የሚያጣምረው አያያዥ ቃል፡

ሀ) ስለዚህ ለ) ይሁን እንጂ

LIVEWORKSHEETS

ሐ) አለበለዚያ                    መ) እና

19. በአንድ ድርሰት ውስጥ የገሃዱን ዓለም መስለው የሚጫወቱ አካላት ምን ይባላሉ?

ሀ) ደራስያን    ለ) ገፀ ባህርያት    ሐ) አንባቢያን    መ) ተደራሲ

20. ከሚከተሉት አንዱ ከቃላዊ ግጥም ውስጥ አይመደብም

ሀ) ፋከራ    ለ) ሽለላ

ሐ) የግጥም መድብል    መ) ሙሾ

ኩታ አለባበሱን ማነው ያስተማረሽ፣

ማጣፋቱንማ ታውቂበታለሽ፣

21. የዚህ ቅኔ ወርቅ የቱ ነው?

ሀ) ኩታ አለባበሱን    ለ) የኩታ አለባበሱን ታውቂያለሽ

ሐ) ማገዳደሉን ተክነሽበታል    መ) ማጣፋቱን ታውቂያለሽ

ቸሩ አባታችን ለሁሉም ሲያበላ፣

ይገርማል አንዳንዴ አይሰጥም ከጠላ፣

22. የዚህ ቅኔ ህብረ ቃሉ የቱ ነው ?

ሀ) ለሁሉም    ለ) ከጠላ    ሐ) አይሰጥም    መ) አባታችን

23. አምና ብጠይቅሽ ልጅ ነው ብለሽኛል፣

ዘንድሮ በተራሽ............ የዚህን ቃላዊ የፍቅር ግጥም ሊያሟል የሚችለው ፡

ሀ) ተዝናንተሽብኛል    ለ) ወፋፍረሽብኛል

LIVEWORKSHEETS

ሐ) ተኩራርተሸብኛል　　　　　　　መ) አርጅተሸብኛል

24. **እንጀራ** የሚለው ቃል በፍካሪያዊ ፍቺው የገባው በየትኛው ዓ/ነገር ነው?

ሀ) ልጅቷ እንጀራ እየጋገረች ነው

ለ) እንጀራ በወጥ የኢትዮጵያዊ ምግብ ነው

ሐ) ወንድማችን እንጀራ ፍለጋ ከሀገር ሀገር ይንከራተታል

መ) ዛሬ እንጀራ የመብላት ፍላጎት የለኝም

25. **በተሀ** ለሚለው ቃል ተመሳሳይ

ሀ) የደረቀ ብርዝ　　　　ለ) ያልበሰለ ጠጅ　　　　መ) የበሰለ ጠጅ

26. ከሚከተሉት አንዱ ምልክት ወይም የሚለውን ቃል ይተካል።

ሀ) ፣　　　　ለ) /　　　　ሐ) ( )　　　　መ) ለ እና ሐ

27. ልዩ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ) ውርንጭላ　　　　ለ) ቡችላ　　　　ሐ) ጨቅላ　　　　መ) ሙጭቅሊት

28. ልጅ ጠንክሮ ባለማጥናቱ ፈተና ወደቀ ። በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ምክንያት የሚሆነው ምንድን ነው?

ሀ) ጠንክሮ ካልማጥናቱ　　　　ለ) መውደቅ

ሐ) መስራት　　　　መ) ልጁ

29. መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገሮች ምንድን ናቸው?

ሀ) የሚጠይቁ　　　　ለ) የሚያብራሩ　　　　ሐ) ሐተታዊ　　　　መ) ሁሉም

LIVEWORKSHEETS

30. የደራሲው የምናብ አለም ሰዎች ............. ይባላሉ።

ሀ) መቼት ለ) ግጭት ሐ) ጭብጥ መ) ገፀ ባህሪ

31. እንዲህ ልጠግብ.............................

ሀ) ሆዴን አመመኝ ለ) በሬዬን አረድሁት

ሐ) ገንዘቤን ጨረስኩት ሐ) እቃዬን ሸጥኩት

32. የማይተማመን ባልጀራ............................

ሀ) በየመንገዱ ይቆማል ለ) በየመንገዱ ይማማላል

ሐ) በአንድላይ ይሄዳል መ) ፊትና ኋላ ይሄዳል

33. የግፍ ግፍ....................................

ሀ) ቶሎ አያልፍ ለ) ክልፍ ክልፍ

ሐ) በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ መ) እልፍ እልፍ

34. ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ..................................

ሀ) ያባርሯታል ለ) ይከተሏታል

ሐ) ያርዷታል መ) ጅግራ ናት ይሏታል

35. በሽታውን ያልተናገረ......................................

ሀ) መታከም አይችልም ለ) መድሃኒት አያገኝም

ሐ) መድሃኒት አይገኝለትም መ) መዳን አይችልም

LIVEWORKSHEETS